

# የጳውሎስ የመጀመሪያው የሚሲዮን ጉዞ

- ጳውሎስና በርናባስ በአንፆኪያ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን መምህራን ነበሩ። በአንድ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ መንፈስ ቅዱስ ለሁለቱ ሰዎች ያለውን ልዩ እቅድ ገለጠላቸው። ቤተክርስቲያንም ከፆመችና ከፀለየችላቸው በኋላ ወደሚሄዱበት መንገድ ላከቻቸው።

- መጀመሪያ ወደ ቆጵሮስ ደሴት በጀልባ ተጓዙ። ይህችን ደሴት ካቋረጡ በኋላም ጳፉ ወደተባለች ከተማ ደረሱ። በዚያች ከተማም አስደናቂ ነገር ሆነ። አንድ በርያሱስ የሚባል ጠንቋይ በዚያች ከተማ ይኖር ነበር። በሚሰራቸው ድንቆችም ብዙ ሰዎችን ያሳሳት ነበር። በዚያን ጊዜም በዚያች ከተማ ሰርግዮስ ጳውሎስ በመባል የሚታወቀው አገረ ገዢ የነጳውሎስን ስብከት ሊሰማ ይፈልግ ነበር። በርያሱስ የከተማዋ ገዢ የነጳውሎስን ስብከት እንዲሰማ አልፈለገም። ስለዚህም እነርሱን እየተቃወመ መናገር ጀመረ።

- ጳውሎስም በርያሱስ በሚታወቅበት ኤልማስ በሚባለው በሌላኛው ስሙ ጠርቶት፣ “አንተ የእውነት ሁሉ ጠላትና የዲያቢሎስ ልጅ!” አለው። ቀጥሎም እውር እንደሚሆንና ብርሃን ማየት እንደማይቻለው ነገረው። ሁሉም ነገር ጨለማ ሆነበት። ምንም ነገር ማየት ተሳነው። ወዲያውም በእጁ ይዞ የሚመራው ሰው መፈለግ ጀመረ።

- ባለስልጣኑም የሆነውን ነገር ሲመለከት የጳውሎስንና የበርናባስን ትምህርት ተቀበለ። በኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክም እጅግ በጣም ተገረመ።

- ሁለቱ ሚሲዮናውያንም ጉዟቸውን ቀጠሉ። በዚያን ዘመን መኪና፣ ባቡር ወይንም አውቶቡስ የሚታሰብ ነገር አልነበረም። የነበረው አማራጭ በእግር መጓዝ ወይንም እንስሳትን መጋለብ ብቻ ነበር። እጅግ በብዙ ኪሎ ሜትሮች የሚቆጠር ርቀት እየተጓዙ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምሩ ነበር። ብዙ ሰዎችም የእነርሱን ስብከት ከሰሙ በኋላ አምነው የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ይሆኑ ነበር። በዚህ አገልግሎታቸውም ከመጠን በላይ የሆኑ ችግሮችንና ስደቶችን አይተዋል። ሆኖም እነኝህን ችግሮችና ስደቶች መንፈስ ቅዱስንና ጌታ ኢየሱስን በመታዘዝ ከሚገኘው ደስታ ጋር ሲያወዳድሯቸው ከቁጥር የሚገቡ አልነበሩም። አሁን የሚኖሩት ለራሳቸው ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነበር።

ይህ የጳውሎስ የመጀመሪያው ሚሺነሪ ጉዞ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13፡ 1 – 52 ውስጥ ነው።